አፍሪካ ቲቪ

13

# አፍሪካ አካዳሚ

AFRICA ACADEMY

www.AfricaAcademy.com

## ሁሉም ሙስሊም ማወቅ ያለበት አዝካር ፣ ዱዓዕ እና ከፍተኛ ምንዳ ያላቸው ሥራዎች 5

በቴሌግራም

AAcademyEthio

www.AfricaAcademy.com

| | ተግባሩ | ከነቢዩ ሙሐመድ (ﷺ) የተነገረለት መረጃው |
|---|---|---|
| 74 | ከመንገድ ላይ እንቅፋትን ማስወገድ | አንድ ሰው ሰዎችን በመንገድ ላይ ስታስቸግር የነበረችን ዛፍ በመቁረጡ ምክኒያት ብቻ በጀነት ውስጥ ሲደሰት አየሁት፡፡ |
| 75 | ክርክርንና ውሸትን መተው | በእውነትም ቢሆን ክርክርን ለተወ ሰው በጀነት ዳርቻ ላይ ቤት እንደሚኖረው ዋስትና እገባለሁ፡፡ እየቀለደም ቢሆን ውሸትን ለተወ ሰው በጀነት ውስጥ ቤት እንደሚኖረው ዋስትና እገባለሁ፡፡ |
| 76 | ቁጣውን የተቆጣጠረ ሰው | መተግበር እየቻለ ቁጣውን የተቆጣጠረ ሰው አላህ የቂያም ቀን በህዝቦች መካከል ጠርቶ ከሁሩል ዐይኖች ያማርጠዋል፡፡ |
| 77 | ኸይር የተወራለት ሰው | ኸይር ያወራችሁለት ሰው ጀነት ለእሱ ናት፡፡ መጥፎ ያወራችሁበት ሰው ደግሞ እሳት ለእሱ ናት፡፡ ምክኒያቱም እናንተ በምድር ላይ የአላህ ምስክሮች ናችሁና፡፡ |

| | | |
|---|---|---|
| 78 | የሙስሊምን ችግር ያቃለለ፤ የደበቀና የተባበረው | ከሙስሊሞች የዱንያ ችግር ያቃለለ ሰው አላህ ከመጭው አለም ችግሩ ያቃልለታል፡፡ በተቸገረ ላይ ያግራራ ሰው በዱንያም ሆነ በመጭው አለም ያቀልልለታል፡፡ የሙስሊምን ነውር የደበቀ በዱንያም ሆነ በመጭው አለም አላህ ነውሩን ይደብቅለታል፡፡ አንድ ሰው ሙስሊም ወንድሙን እስከተባበረ ድረስ አላህ እርሱን ከማገዝ አይወገድም፡፡(አይቆጠብም) |
| 79 | ጭንቀቱ አኺራው የሆነ | የሆነለት ሰው ክብረቱን አሏህ በልቡ ውስጥ ያደርግለታል፡፡ ሐሳቡን ይሰበስብለታል፡፡ ዱንያም በግዷ ትመጣለታለች፡፡ |
| 80 | ፍትሃዊ አስተዳደሪ (መልካም ወጣት) ከመስጂድ ጋር መቆራኘት (ለአላህ ብሎ መውደድ) | አላህ የእሱ ጥላ እንጂ ሌላ ጥላ በሌለበት ጊዜ ሰባት ሰዎችን በጥላው ስር ያውሳቸዋል፡፡ ፍትሃዊ አስተዳዳሪ፣ በጌታው አምልኮ ተከትኩቶ ያደገ ወጣት፤ ልቡ ከመስጊድ ጋር የተሳሰረ ሰው፤ ለአላህ ብለው የተዋደዱ፤ ቆንጆና ባለስልጣን ሴት የጠየቀችውና እኔ አላህን እፈራለሁ ያ ሰው፤ ቀኝ እጁ የሚሰጠውን ግራ እጁ እስከማያውቀው ድረስ ስጦታውን የሚደብቅ፤ ብቻውን ባለበት አላህን አስታውሶ እንባው የረገፈለት ሰው ናቸው፡፡ |
| 81 | ኢስቲግፋር ማብዛት | ኢስቲግፋር ያበዛ ሰው ለሚያጣብበው ሁሉ መውጫ ያደርግለታል፡፡ ለሚያስጨንቀው ሁሉ መፍትሄ ይሰጠዋል፡፡ ካላሰበ በኩል ይመግበዋል (ሲሳይን) ያመጣለታል፡፡ |


AAcademyEthio
www.AfricaAcademy.com

# እውቀት ተግባርን ስለ መጠየቁ

- ያለ ተግባር እውቀት ብቻ በአላህ፤ በመልዕክተኛውና በሙስሊሞች ዘንድ የተወገዘ ነው፡፡
- አሏህም እንዲህ ይላል፡- (የማትሰሩት ነገር መናገራችሁ አላህ ዘንድ በመጠላት ተለቀ (እጅግ ከበደ)፡፡)
- አቡሁረይራ (ያ! የማይሰራበት እውቀት ምሳሌው ባአሏህ መንገድ ላይ ምንም የማይሰጥበት የገንዘብ ድልብ አይነት ነው፡፡) ብለዋል፡፡
- ፉዴይል ኢብኑ ዒያድ የተባሉ ዐሊም፡- (ረሂመሁሏህ) (አንድ ሰው ባወቀው እስከሚተገብር ድረስ ከአላዋቂዎች ነው የሚመደበው) ብለዋል፡፡
- ማሊክ ቢን ዲናር (ረሁመሁሏህ)፡- (አንድም ፊደል ስህተት የሌለው ሆኖ ተግባሩ ግን ሁሉም ስህተት የሆነ ሰው አለ) ብለዋል፡፡

- ስለዚህ ሙስሊም ወንድሜና ሙስሊም እህቴ! አያሌ ጥቅም ያዘለውን ይህንን መፅሐፍ ለማንበብ አላህ (ﷻ) አግርቶላችኋል፡፡ የቀረውም የንባብ ውጤት የሆነው ነው፡፡ ይኸውም በእሱ መሠረት ህይወትን መምራት ነው፡፡ አያ የቁርአን አንቀፆችና ተፍሲሮቻቸው አልፈውልሃል፡፡ እናም በተረዳኸው የቁርአን ምክር ተመከር፡፡

- የነቢዩ ሙሐመድ ባልደረቦች ከነቢዩ ሙሐመድ (ﷺ) አስር አንቀፅን ይማሩና ወደ ሌሎች አስርት አናቅፅ ከመተላለፋቸው በፊት የእነዚህን መልእክትና ተግባር ነበር የሚያስቀድሙት፡፡ እውቀትንም ተግባርንም በአንድ ጎን ለጎን ተማርን ይሉ ነበር፡፡ የኢስላም መመሪያ በዚሁ ላይ ነው የሚገፋፋው፡፡

- ኢብኑ ዐባስ (يَتْلُونَهُ حَقَّ تِلَاوَتِهِ)(አግባብነት ያለውን ንባብ ያነቡታል)፡፡

የሚለውን አንቀፅ ሲተረጉሙ፡- በትክክል የሚከተሉት ማለት ነው ሲሉ ፉዶይል ደግሞ ቁርአን የተወረደው ሊሰራበት ሲሆን ሰዎች ግን ማንበቡን እንደ ትልቅ ስራ አድርገው ያዙት ብለዋል፡፡



AAcademyEthio
www.AfricaAcademy.com

- ከነቢዩ ሙሐመድ (ﷺ) ሱናዎችና ሐዲሶች ቀደም ባሉት ትምህርቶች የተወሰኑ አልፈዋል፡፡
- በእነሱም ለማዘዝና በእርሱ ለመስራት ተዘጋጅ፡፡
- ስመ ጥሩ ሰዎች ሁሉ አንድን ነገር ባወቁ ቁጥር ነቢዩ ሙሐመድ (ﷺ) ቡኻሪና ሙስሊም በዘገቡት ሐዲስ (በአንድ ነገር ሳዛችሁ የአቅማችሁን ያህል ተግብሩት የከለከልኳችሁን ግን ሁሉንም ተውት፡፡)
- ያሉትን መመሪያ ለማክበር ብለውና አላህ (እነዚያ ትእዛዙን የሚጥሱ ሰዎች በዱንያ መከራ እንዳትደርስባቸው ወይም በአኺራ አሳማሚ ቅጣት እንዳያገኛቸው ይጠንቀቁ በማለት የተናገረውን ለመተግበር አቅማችሁ በፈቀደው ልክ ሲሯሯጡና ሰዎችንም ወደዚያው ተግባር ለመጥራት ሲጣደፉ ነበር የሚውሉት፡፡

- በዚህ ጉዳይ ሞዴል ከፍተኛ አርአያ ነበሩ ከሚባሉት ሰዎች መካከል፡-
- ከነቢዩ (ﷺ) ሙስሊም በዘገቡት ሐዲስ (በቀንና በሌሊት አስራ ሁለት ረከዐ የሰገደ ሰው በእነዚህ ምክንያት በጀነት ውስጥ ቤት ይገነባለታል) ተብሏል፡፡ ይህን ሐዲስ ከነቢዩ (ﷺ) ያወሩት እናታችን ኡሙ ሐቢባ፡- (ይህን ሐዲስ ከሰማሁኝ ጀምሮ አንድም ቀን አልተውኳቸውም) ይላሉ፡፡
- (አንድ ሙስሊም ኑዛዜ ማድረግ ያለበትን ነገር ሳይናዘዝ ሶስት ሌሊት ሊያልፈው አይገባል) የሚለውን ሐዲስ ያወሩት ታላቁ ሱሐቢ ዐብደላህ ኢብኑ ዑመር፡- አንድም ቀን ኑዛዜ ሳላደርግ አድሬ አላውቅም ብለዋል፡፡
- ታላቁ ኢማም አህመድ ቢን ሐንበል (አንድም ሐዲስ ፅፌ አላውቅም፤ የተገበርኩት ቢሆን እንጂ፡፡ ነቢዩ ደግመው ለአቡ ጠይባ አንድ ዲናር ሰጡ የሚለውን ሐዲስ ስሰማ
ደግሜ አንድ ዲናር ሰጠሁ፡፡) ብለዋል፡፡

- ታላቁ ኢማም ቡኻሪም እንዲህ ብለው ነበር (ሐሜት ሐራም መሆኑን ከሰማሁ ጀምሬ አንድም ቀን አምቼ አላውቅም፡፡ አንድንም ሰው አምተሃል ብሎ እንደማይመረምረኝ አላህን ተስፋ አደርጋለሁ፡፡)

- ነሳኢ የዘገቡት ሐዲስ (ከየሰላት በኋላ አያተል ኩርሲን ያነበበ ሰው ጀነት ከመግባት ከሞት በስተቀር የሚከለክለው ነገር የለም) ይላል፡፡ ኢብኑል ቀይም ስለዚህ ጉዳይ ሲናገሩ፡- ኢብኑ ተይሚያ (ረስቼ ወይም በሌላ ችግር ምክንያት ካልሆነ በስተቀር ከሶላት በኋላ አያተል ኩርሲን አንድም ቀን ትቻት አላውቅም፡፡) ብለዋል፡፡

- ከማወቅና ከመተግበር ቀጥሎ ሌሎችም በዚሁ አይነት እንዲህ ካሉ፣ ወደ እዚሁ አላህ ወደ ዋለልህ ፀጋ መጥራትና እራስህንም ሆነ ሌሎችን የኸይር ተካፋይ እንዲሆኑ ማድረግ አማራጭ የሌለው ጉዳይ ነው፡፡

- ነቢዩ ሙሐመድ (ﷺ) ሙስሊም በዘገቡት ሐዲስ (ኸይርን ያሳየ ሰው የስራው ሰው የሚያገኘውን ምንዳ ያህል ያገኛል) ብለዋል፡፡
- ቡኻሪ በዘገቡት ሐዲስ (ከናንተ በላጫችሁ ቁርአንን ተምሮ ያስተማረው ሰው ነው) ብለዋል፡፡
- ቡኻሪና ሙስሊም በዘገቡት ሐዲስ (ከእኔ የሰማችሁትን አንድም አንቀፅ ቢሆን ላልሰማ አሰሙ) ብለዋል፡፡
- ወንድሜ ሆይ! ኸይር ነገርን ባስፋፋህ ልክ አጅርህ ይበዛል፡፡ በህይወት እያለህም ሆነ ከሞትክ በኋላ ምንዳህ ይበረክታል፡፡ ስለዚህ ጉዳይ ነቢዩ ሙሐመድ (ﷺ) ሙስሊም በዘገቡት ሐዲስ (አንድ ሰው ሲሞት ከሶስት ነገር ሌላ የሆነው ተግባሩ ሁሉ ይቋረጣል፡፡ እነሱም ቀጣይነት ያላት ሰደቃ፣ ሌሎች የሚጠቀሙበት ትምህርት፣ ለእሱ ዱዓ የሚያደርግለት መልካም ልጅ) ብለዋል፡፡

- ማብራሪያ፡- እኛ ሙስሊሞች በየቀኑ ከአስራ ሰባት ጊዜ በላይ የፈቲሀን ምዕራፍ እናነባታለን፡፡ በዚህም ጊዜ አላህ ከተቆጣባቸውና ከተሳሳቱት ሰዎች ተግባር በእሱ እንጠበቃለን፡፡ በተግባር ግን እነሱን እንመስላለን፡፡ ምክኒያቱም አንዳዶቻችን ሳንማር በድንቁርና ተውጠን ወደ ስራ እንገባና በተግባራችን የተሳሳቱትን ክርስቲያኖች እንመስላለን፡፡ ሌሎቻችን ደግሞ እንማርና ባወቅነው መሠረት ባለመተግበር እነዚያ አላህ የተቆጣባቸውን አይሁድ እንመስላለን፡፡ ለእኛም ሆነ ለአንተ እውቀትንና ተግባርን በአንድ እንዲሰጠን አላህን እንማፀነዋለን፡፡
- ትክክለኛውን አላህና መልዕክተኛው ብቻ ያውቃሉ፡፡
- አላህ በነቢያችን፡ በቤተሰቦቻቸውና በሁሉም ጓዶቻቸው ሰላሙንና ርህራሄውን ያወርድላቸው!



AAcademyEthio
www.AfricaAcademy.com